

የተባበሩት መንግስታት የልጆች መብቶች ኮንቪንሽን እንደሚለው፣ ልጅ የሚባለው የአዋቂነት ዕድሜ ላይ ያልደረሰ ማንኛውም ሰው ነው። እኛ ልጆች፣ መብቶቻችንን የማወቅ መብት አለን። ሁሉም ሀገሮች የልጆችን መብቶች ማክበር እና የእኛን የወደፊት ፍላጎታችንን ማስጠበቅ ይገባቸዋል።



እኛ ልጆች፣ በህይወት የመኖርና የመበልፀግ መብት አለን።
የበቂ ምግብ እና ንፅህ የሆነ መጠጥ ውሃ የማግኘት መብት አለን።




ያለንበት ቦታ የትም ቢሆን ፣ ስንወለድ ስም የማግኘት እና ዜግነት የማግኘት መብት አለን።



እኛ ልጆች፣ ከወላጆቻችን፣ ቤተሰቦቻችን፣ ከሚንከባከቡን ሰዎች ጋር የመኖር መብት አለን።



በጾታ፣ በዘር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ ወይም በጎሳ ማንም ሰው በልጆች ላይ አድልዎ የማድረግ መብት የለውም።



እኛ ልጆች፣ የትምህርት እና ነፃ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የማግኘት መብት አለን።



እኛ ልጆችን ስሙን ሀሳባችንን የመግለፅ መብት አለን።



እኛ ልጆች፣ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን የማግኘት መብት አለን።




ልዩ ፍላጎት ያላቸው ልጆች ልዩ እንክብካቤ የማግኘት መብት አላቸው።




እኛ ልጆች ስደተኞች ወይም በሦስተኛ ሀገሮች ውስጥ የምንኖር የውጭ ሀገር ነዋሪዎች ከሆንን፣ ተገቢ እንክብካቤ እና ጥበቃ የማግኘት መብት አለን።



እኛ ልጆች እረፍት የማግኘት ፣ የመጫወት እና በመዝናኛ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመሳተፍ መብት አለን።



እኛ ልጆች፣ ከሁሉም ዓይነት ግፍና አድልዎ የመጠበቅ መብት አለን።



እኛ ልጆች፣ በተለይም በመማሪያ ዘመናችን እንደ ርካሽ የሰው ኃይል ልናገለግል አይገባም።

